የአስተዳደር ሕግ፡ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በዳኝነት አካላት ስለመከለስ

የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማእከል

የዳኞች እና የዐቃብያነሕግ ስልጠና ፕሮግራም

መጋቢት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማው ጫ **ገጽ**

I. መግቢያ 1

ክፍል አንድ..... 3

1. የአስተዳደር ሕግ አጠቃላይ..... 3

1.1 የአስተዳደር ሕግ ምንነትና ዓለማዉ..... 3

1.2 የአስተዳደር ሕግ ይዘት..... 4

1.3 የአስተዳደር ሕግና ሕገ መንግስት..... 7

1.3.1 የአስተዳደር ሕግ የሚመለከታቸዉ የሕገ መንግስት መርሆዎች..... 7

1.4 የአስተዳደር አካላትን ዉሳኔዎች የመከስ የፍ/ቤቶች ስልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት..... 11

የመወያያ ጥያቄዎች..... 12

ክፍል ሁለት..... 13

2. የአስተዳደር ውሳኔዎችን በዳኝነት አካል የመከለስ (Judicial Review)

አጠቃላይ መርሆዎች..... 13

2.1 ከመደበኛ የዳኝነት አካላት ውጭ በሚገኝ እራሱን በቻለ የአስተዳደር ፍርድ ቤት የሚከለስበት ሁኔታ..... 15

2.2 በመደበኛ የዳኝነት አካል ውስጥ በሚገኝ የአስተዳደር ጉዳይ ልዩ ችሎት ክለሳ ስለሚደረግበት ሁኔታ 17

2.3 በመደበኛ የዳኝነት አካል የአስተዳደር ውሳኔ ክለሳ ስለሚደረግበት ሁኔታ 19

የመወያያ ጥያቄዎች..... 20

ክፍል ሶስት..... 22

3. የአስተዳደር አካላትን ውሳኔዎች የመከለስ የፍርድ ቤቶች ስልጣን
እና በአገራችን ስላለው አፈጻጸም 22

3.1 የመከለስ ስልጣን ለፍርድ ቤቶች በሕግ በግልጽ የተሰጠባቸው ሁኔታዎች..... 23

የመወያያ ጥያቄዎች..... 27

3.2 የመከለስ ስልጣን ለፍርድ ቤቶች በሕግ በግልጽ ባልተሰጠ ጊዜ ስላለ ሁኔታ... 28

የመወያያ ጥያቄዎች..... 32

ክፍል አራት..... 33

4. የአስተዳደር ውሳኔዎችን የመከለስ አፈጻጸም እና አተረጓጎም ላይ

የሚታዩ ችግሮች 33

የመወያያ ጥያቄዎች..... 35

5. ማጠቃለያ..... 36

II. ዋቢ ጽሁፎች..... 38

I. <u>መግቢያ</u>

መንግስታት ቀደም ሲል ለረጅም ጊዜያት እንደ ዋነኛ ስራቸው አድርገው የያዙት የአገርን ድንበር የመጠበቅ እና በሚያስተዳድሩት አገር ድንበር ውስጥ ሕግና ስርዓት የማስከበር ተግባር እንደነበር ከታሪክ ድርሳናት ለመረዳት ይቻላል። የዚህ ዓይነቶቹ መንግስታት ከጊዜ በኋላ በአገራቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ጉልህ ሚና በመጫወት የዜጎቻቸውን ህይወት ለማሻሻል በሚሰሩ መንግስታት (Welfare Governments) መተካት ከጀመሩ ውሎ አድሯል።

በሃያኛው ክፍለዘመን በተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚገኙ መንግስታት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የመጣውን የዜጎቻቸውን ኢኮኖሚ፣ጤና፣ ደህንነት፣ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ወ.ዘ.ተ የሚመለከቱ ኃላፊነቶቻቸውን ለመወጣት በርካታ ሕጎችን እና ሕጎቹን የሚያስፈጽሙ የአስተዳደር አካላትን የማቋቋሙን ስራ በሰፊው አከናውነዋል። በአሁኑም ወቅት መንግስታት እየገቡበት ካለው የስራ መስክ ስፋት እና ከዘመናዊ ሕብረተሰብ ውስብስብነት አንጻር ህግ አውጪ አካላት በሚያወጧቸው ህጎች ሁሉም ጉዳዮች ላይ በዝርዝር መደንገግ ወደማይችሉበት ደረጃ በመድረሳቸው የተወሰኑ መርሆዎችን በህጎቹ በማካተት ሕጎቹን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላት ምክንያታዊ ነው በሚሉት ሁኔታ ስራ ላይ የሚያውሉት እንደሁኔታው የሚጠቀሙበት ሥልጣን (Discretionary power) የሚሰጡበት ሁኔታም በተለያዩ ሕግጋት ውስጥ የሚገኝ እውነታ ነው።

በተጠቀሰው ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ የመጡት የአስተዳደር አካላት ባቋቋሚቸው ሕጎችና በሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች መሰረት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን እንዲሁም ከስልጣናቸው በማለፍ የዜጎችን መብቶች እንዳይነኩ የተለያዩ የቁጥጥር ስርዓቶች በተለያዩ የህግ ስርዓቶች ተዘርግተዋል። በአጠቃላይ የቁጥጥር ስርዓቶቹ ውስጣዊና ውጫዊ በመባል በሁለት ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ሲሆን የመጀመሪያው የአስተዳደር አካላቱ በራሳቸው የውስጥ አሰራር የሚያደርጉትን ቁጥጥር የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው የቁጥጥር ዓይነት ደግሞ በሕግ አውጭው ክፍል፣ በእንባጠባቂ ተቋም፣ ከመደበኛው የዳኝነት አካላት ውጭ ባሉ የአስተዳደር ትሪቡናልስ (Administrative Tribunals) እንዲሁም የአስተዳደር አካላት ውሳኔዎች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚከለሱበትን ሁኔታ (Judicial review) የሚያጠቃልል ነው።

የአስተዳደር ሕግ የተለያዩ የመንግስት አስተዳደር አካላት በሕግ የተጣሉባቸውን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በዋነኛነት የሚገዛ የመንግስት ሕግ(Public Law) ክፍል ነው። ይህ ክፍለ ትምህርት የአስተዳደር አካላት በተቋቋሙበት ሕግ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚወጡበት ሂደት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች የዳኝነት አካላት በመከለስ ቁጥጥር በሚያደርጉበት ሁኔታ ላይ ትኩረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

በክፍለ ትምህርቱ(Module) የመጀመሪያ ምዕራፍ ለአስተዳደር ሕግ መሰረት ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት ድንጋጌዎችን እና መርሆዎችን ለመዳሰስ ይሞክራል። በጽሁፉ ሁለተኛ ምዕራፍ የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች የዳኝነት አካላት በመከለስ እንዳስፈላጊነቱ ለማረም በመመዘኛነት ሊጠቀሙባቸው ስለሚገቡ መርሆዎች እናያለን። ለዚሁ ተግባር በአስተዳደር ሕግ የዳበረ ልምድ እንዳላቸው የሚታመኑ የተለያየ የሕግ ስርዓት የሚከተሉ የተወሰኑ አገሮች ልምድ ባጭሩ ይዳሰሳል። በጽሁፉ ሶስተኛ ክፍል በአገራችን የአስተዳደር አካላትን ውሳኔዎች በዳኝነት የሚከለሱበትን ሁኔታ በተመለከተ የሚታዩ አሰራሮችን እና ለዳኝነት አካላት ስልጣን የሚሰጡ አግባብነት ያላቸው የተወሰኑ አዋጆች ለግንዛቤ እንዲረዳ ይታያሉ። በክፍል አራት ስር የዳኝነት አካላት የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በሚከልሱበት ወቅት በአፈጻጸም ስለሚታዩ ችግሮች ለማየት ይሞክራል። በመጨረሻም በተቻለ መጠን የተለያዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች (በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ጨምሮ) የተሰጡ ውሳኔዎችን መነሻ በማድረግ የዳኝነት አካላት የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በሚከልሱበት ጊዜ ሊከተሏቸው የሚገቡ የተሻሉ የሚባሉ አሰራሮችን በመጠቆም ጽሁፉ ይጠቃለላል።

በተጨማሪ በእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ላይ በየርዕሱ ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖር እገዛ እንደሚያደርጉ የታመነባቸው የመወያያ ጥያቄዎች ተካተዋል።

ክፍል አንድ

1. የአስተዳደር ሕግ አጠቃላይ መርሆዎች

የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል ተከታትለው ሲያጠናቅቁ፡-

- ከአስተዳደር ሕግ ጋር የሚገናኙ የኢፌዲሪ ሕገመንግስት የተወሰኑ ድንጋጌዎችን ይለያሉ፤
- በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የተረጋገጡ የዜጎችን መብት ከማስከበር አንጻር የአስተዳደር ሕግ ያለውን ሚና ይረዳሉ፤
- የአስተዳደር ሕግ ከሕገመንግስቱ ጋር ያለውን ግንኙነት የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ በኩል ስላለው ሚና በመረዳት ለተግባራዊነቱ ይሰራሉ፡፡

1.1. የአስተዳደር ህግ ምንነትና ዓለማው

የአስተዳደር ህግ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እስከ አሁን በቂ ትርጉም ባይቀመጥለትም አንዳንድ ፀሐፊዎች የየበኩላቸውን ትርጉም ለመስጠት ሞክረዋል፡፡

ሰር አይደኤንግ የተባለ የኢንግሊዝ ፀሐፊ የአስተዳደር ህግ የአስተዳደር አካላትን የሚመለከት ሆኖ የአስተዳደር አካላትን አደረጃጀት ስልጣንና ኃላፊነትን የሚወስን ህግ ነው በማለት አስቀምጧል፡፡

ዳይሲ የሚባል የእንግሊዝ ፀሐፊ ደግሞ የአስተዳደር ህግ የመንግስት ባለስልጣናትን ወይም ኃላፊዎችን የህግ ኃላፊነታቸውን የሚወስን ግለሰቦች ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ባላቸው ግንኙነት ግዴታቸውን የሚያፈጽሙበት ስርዓት የሚመለከት ነው ብሎአል፡፡

ዋድ የሚባል ፀሐፊ ደግሞ የአስተዳደር ህግ የአስተዳደር አካላትን ተግባርና ስልጣንን የሚቆጣጠር ህግ ነው ብሎአል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሸዋረዝ የሚባል ፀሐፊ የአስተዳደር ህግ የመንግስት አስተዳደር ስራን የሚቆጣጠር የህግ ክፍል ነው በማለት አስቀምጧል፡፡

ከነዚህ ትርጉም መረዳት የሚቻለው የአስተዳደር ህግ ማለት የአስተዳደር አካላትን ተግባርና ስልጣናቸውን የሚመለከት ህግ ሆኖ በስልጣናቸው በሚሰሩበት ጊዜ ሊከተሉቸአው የሚገባውን

ህግጋት የስልጣናቸውን ቁጥጥርና ግለሰቦች ከአስተዳደር አካላት ጋር ባለቸው ግንኙነት ያላቸውን መብት የሚያመለክት ህግ መሆኑን ነው።

በመሆኑም የአስተዳደር ህግ ዋና ዓለማ የአስተዳደር አካላትን ስልጣን መቆጣጠር ነው። የአስተዳደር ህግ ዜጎች ከመንግስት ማን አለብኝነት እርምጃ ወይም ህግ ወጥ እርምጃ ይጠብቃል። የመንግስት ባለስልጣናት በግለሰቦች መብት ውስጥ ከህግ ውጭ ጠልቃ እንደይገቡ መጠበቁ የአስተዳደር ህግ ዋናኛ ትኩረት ነው:: ይህ ማለት የአስተዳደር ህግ የአስተዳደር ክፍሉ ያለ አግባብ ወይም ከህግ ውጭ በዜጎች መብት ውስጥ ጠልቃ ሲገቡ ግለሰቦች መብታቸውን የሚያስከብሩበትን ስርዓት በማስቀመጥ የግልሰቦች መብት እንድከበር ያደርጋል ማለት ነው።

የአስተዳደር ህግ የአስተዳደር አካሉ ስልጣን ሚዛናዊ ሆኖ የህዝብ ጥቅም (public interest) ና የግል መብት (Private Right) በተጣጠመ መልኩ ጎን ለጎን ተፈጻሚ የሚሆንበትን ስርዓት የሚያመቻች ነው። የአስተዳደር አካላቱ ስልጣን በህግ መዕቀፍ ቁጥጥር ውስጥ ሲሆን የአስተዳደር አምባገነንነት ወይም ፈላጭ ቆራጭነት ቦታ ስለማይኖረው ስልጣኑ በህግ ስርዓት ይመራል። የግለሰቦች መብት በሕግ የሚከበርበት የህግ የበላይነት ስርዓት ይሰፍናል። በመሆኑም የአስተዳደር ህግ መሰረታዊ ዓለማ የግለሰቦችን መብት በህግ በማስከበር የህግ የበላይነት ስርዓትን ማስፈንና ማረጋገጥ ነው።

1.2. <u>የአስተዳደር ህግ ይዘት</u>

የአስተዳደር ህግ ሁሉንም የመንግስት ስራ የሚመለከት ሳይሆን በውስን ጉዳዮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ነው። ከዚህም የተነሳ የአስተዳደር ህግ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች በዚህ ርዕስ ስር እንመለከታለን።

የአስተዳደር ህግ የመጀመሪያው ይዘት የአስተዳደር አካላትን አደረጃጀት ስልጣንና ተግባራቸውን የሚመለከት ነው። ባለንበት ዘመን አስተዳደር ክፍል ሰፊ የመንግስትን ስልጣን አላቸው። በርካታ ተግባራትንም ያከናውነሉ።
የአስተዳደር አካላትን ስልጣንና ተግባር በሦስት ከፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

ሀ. <u>የማስተዳደር ወይም የማስፈጸም ስልጣን</u>

በዘመናዊ የመንግስት ስርዓት ውስጥ የመንግስት ስልጣን ህግ አውጭ፣ ህግ ተርጓሚ፣ ህግ አስፈፃሚ በመባል በሦስት የሚከፈል ሲሆን ለህግ አውጭና ህግ ተርጓሚ የመንግስት ክፍሎች ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የሆነው የመንግስት ተግባር ለአስፈፃሚው ወይም ለአስተዳደሩ የመንግስት ክፍል የሚሰጥ ነው።

የአስተዳደር አካላት በማስተዳደሩ ወይም ህግን በማስፈጸሙ ተግባራቸው ውስጥ ሰፊ የሆነ የመሰላቸውን የመወሰን ስልጣን (Discretion) ያላቸው ሲሆን በተግባራቸው ውስጥ የሚያጋጥሙአቸውን ጉዳዮች ከሉት አማራጭ መፍትሖች ይሻላል የሚሉትን መርጠው የመከተል ወይም የመስረት ስልጣን አላቸው። ይህ ስልጣናቸው ግን በህግ መዕቀፍ ውስጥ የሚከናወን ካልሆነ በስተቀር የአስተዳደሩ ክፍል በቀላሉ አምባገነን በመሆን ዜጎችን የሚጨቁኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ይህ በመሆኑም ነው የአስተዳደር ህግ ያስፈለገው።

ለ. <u>በክፍል ህግ የማውጣት ስልጣን</u>

የአስተዳደሩ ክፍል ከማስተዳደር ስራቸው ወይም ስልጣናቸው ጎን ለጎን ህግ የማውጣት ስልጣንም ስሰጣቸው ይስተዋለል። ይህ ስልጣን ህግ የማውጣት ክፍል ሰልጣን (quasi legislative power) በመባል ይታወቃል። ህግ የማውጣት ስልጣን መሰረታዊ የአስተዳደር ክፍል ስልጣን ሳይሆን ህግ አውጭው ክፍል የሚሰጣቸው የውክልና ስልጣን ነው። የአስተዳደሩ ክፍል ከህግ አውጭው የመንግስት ክፍል በሚያገኙት የውክልና ስልጣን ህጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣሉ። ይህ ስልጣናቸው የውክልና ስልጣናቸው ስለ ሆነ በህግ አውጭው ቁጥጥር ስር የሚከናወን ነው።

ሐ. <u>በክፍል የመዳኘት ስልጣን</u>

ለአስተዳደሩ ክፍል በክፍል የመዳኘት ስልጣን መስጠትም በአሁኑ ጊዜ እየተለመደ መጥቷል። የአስተዳደሩ ክፍል በክፍል የመዳኘት ስልጣናቸው (quasi judicial power) ከአስተዳደሩ ክፍሎች ጋር የሚነሳውን የመብት ክርክር ላይ የመወሰን ስልጣን አላቸው።

ሁለተኛው የአስተዳደር ህግ ይዘት የአስተዳደር አካላት ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሊከተሉአቸው የሚገባውን ስርዓት የሚመለከት ነው።

የአስተዳደር አካላት በስልጣናቸው ክልል ውስጥ ምንም እንኳን የመሰላቸውን መርጠው የመወሰን ስልጣን ያላቸው ቢሆንም ከዚህ በላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የመሰላቸውን የመወሰን ሰፊ ስልጣናቸው በመጠቀም አምባገነን እንዳይሆኑ ውሳኔአቸውን በሚወስኑበት ወቅት ልከተሉአቸው የሚገባቸውን መሰረታዊ ስርዓቶች የአስተዳደር ህግ ይወስናል። ከነዚህም ስርዓቶች ውስጥ የፍትሐዊነት ስርዓት (fair justice) ትልቁን ሰፊራ የሚወስድ ነው። ይህ ፍትሐዊ ሰርዓት የተፈጥሮ ፍትህ የመሰማት መብትና ምክንያተዊ ውሳኔን የመወሰን ስርዓትን የሚመለከት ነው።

ሦስተኛው የአስተዳደር ህግ ይዘት የአስተዳደር አካላት ስልጣን ቁጥጥር የሚደረግበትን ስርዓት የሚመለከት ነው።
የአስተዳደር አካላት ባለቸው የመሰላቸውን መርጠው የመወሰን ስልጣን (discretionary power) አምባገነን ወይም ፈላጭ ቆራጭ ሆነው የግለሰቦችን መብት እንዳይጥሱ የተለያዩ የቁጥጥር ስርዓቶች ተዘርግቷል።

ከእነዚህም የቁጥጥር ስርዓቶች የመጀመሪያው በህግ አውጭው የሚደረግ ቁጥጥር (parliamentary control) በመባል ይታወቃል። በዚህ ቁጥጥር ስርዓት ውስጥ ህግ አውጭው የመንግስት ክፍል የአስተዳደር ክፍሉ በህግ ስርዓት ስራውን እንዲያከናውን ህግ ያወጣለታል። የአስተዳደር ክፍሉም ህግ አውጭው የሚያወጣውን ህግ ሳይጥስ ወይም ከህግ ውጭ ሳይሆን ስራውን ይሰራል። በሚወጣው ህግ መሰረት ህግ አውጭው የአስተዳደሩ ክፍል ስራዎቹን በመስመልከት ሪፖርት እንዲያቀርብ በማድረግ እርምቶችን ይሰጣል።

ሌላኛው የቁጥጥር ስርዓት የዚህ ጽሑፍ ትኩረት የሆነው በዳኝነቱ አካል የሚደረግ ቁጥጥር ነው። ይህ ስርዓት የአስተዳደር አካላት ውሳኔዎች በመደበኛ የዳኝነት አካል የሚከለስበት ስርዓት (Judicial Review of Administrative acts) በመባል ይታወቃል።

የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ሌለኛው የመንግስት ክፍል በሆነው የዳኝነት አካል የሚከለሰው እንደ መደባኛ ስራ ሳይሆን በጠበብ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ነው። ይኸውም የአስተዳደሩ ክፍል ውሳኔ የህግ ስርዓትን ያልተከተለ ወይም ሕግን የጣሰ ሲሆን ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዳኝነቱ

አካል የአስተዳደሩን አካል ተክቶ የሚሰራ ወይም በአስተዳደሩ አካል ላይ መሰልጠን ሳይሆን የአስተዳደሩን አካል ውሳኔዎች ሕጋዊነት የሚከታተል ብቻ ነው።

እነዚህ የቁጥጥር ስርዓቶች በሰፊው ተግባር ላይ ያሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአስተዳደሩ ክፍል ውስጥ የህግ ስርዓትን ባለመከተል የሚሰጡትን የግለሰቦች መብት የሚከታተሉ ተቋማትን ማቋቋም እየተለመደ መጥቷል። እነዚህም ተቋማት ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እንባ ጠበቂ ተቋም ፀረ ሙስና ኮሚሽን የመሳሰሉት ናቸው።

1.3. <u>የአስተዳደር ሕግና ሕገ-መንግስት</u>

የአስተዳደር ህግ እና ህገ መንግስት ጥብቅ ግንኙነት ያላቸው የህግ ክፍሎች ናቸው። ከዚህም የተነሳ የአስተዳደር ህግ እንደ ህገ መንግስታዊ ህግ ክፍል ተደርጎ ይወሰደል። የአስተዳደር ህግ መሰረታዊ የሆኑ የህገ መንግስት ይዘቶች ላይ ያነጣጠረ ነው።

1.3.1. <u>የአስተዳደር ህግ የሚመለከታቸው መሰረታዊ የህገ መንግስት መርሆዎች</u>

ዘመናዊ ወይም ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ሊይዛቸው ይገባ ተብሎ የታመነባቸው መሰረታዊ መርሆዎች አሉ። እነዚህም መሰረታዊ መርሆዎች የአንድ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት አምዶች እንደሆኑ ይታመናል። መሰረታዊ የህገ መንግስት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. <u>የህግ የበላይነት</u>

የህግ የባላይነት ማለት በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ስርዓት ማለት ነው። ቀላል ተደርጎ ሲታይ የህግ የበላይነት ማለት ህግ የሚገዛበት ስርዓት ማለት ነው። የህግ የበላይነት ከመንግስት አንፃር ሲታይ በህግ ስርዓት የሚመራ መንግስትን የሚያመለክት ነው። የህግ የበላይነት ስርዓት ዓለማው ግለሰቦች በህግ መሰረት እንዲኖሩ ማድረግ እንዲሁም የመንግስት አካላትን ስልጣን በህግ በመገደብ የግለሰቦችን መብት እንዳይጥሱ በማድረግ የህዝብ ደህንነትን

በማስፈን ፍትህ ማረጋገጥ ነው። ከህግ የበላይነት እሳቤ ጋር ስሙ ሁል ጊዜ የሚነሳው ዳይሲ የሚባል የእንግሊዝ ፀሐፊ የህግ የበላይነትን ምንነት በማስመልከት እስከ ዛሬ ድረስ የዘለቀውን መሪህ አስቀምጧል።

ዳይሲ የህግ የበላይነት ሦስት ይዘቶች እንዳሉት አስቀምጧል። የመጀመሪያው ማንኛውም ሰው ከህግ ውጭ መቀጣት የለበትም የሚል ነው። በዚህ አነጋገር መሰረት ህግ ከልጣሰ በስተቀር ማንኛው ሰው አይቀጣም ማለት ነው። ህግን ከጣሰ ሰው የሚቀጣው በህጉ መሰረት ብቻ ነው።

ሁለተኛው ማንኛውም ሰው በህግ ፊት እኩል ነው ማንም ሰው ከህግ በታች ነው የሚል ነው።

ሦስተኛው የማንኛውም ሰው መብት እና ግዴታ ነፃ በሆነ መደበኛ ፍ/ቤት ነው የሚወሰነው በማለት ዳይሲ ለህግ የበላይነት ትርጉም ሰጥቶአል።

የዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ዓለማ የህግ የበላይነት ስርዓትን ማስፈን ነው። ይህንን በመገንዘብ ይመሰላል በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የመጀመሪያው መግቢያ አንቀጽ ላይ የህገ መንግስቱ ዓለማ በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መገንባት እንደሆነ ተመልክቷል።

የአስተዳደር ህግ ዓለማም የአስተዳደሩ የመንግስት ክፍል ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የግለሰቦችን መብት ሳይጥስ በህግ ስርዓት መዕቀፍ ውስጥ እንዲሰራ ማስቻል ስለሆነ ይህ ዓለማው ከህገ መንግስት ዓለማ ጋር ያመሳስለዋል።

ለ. <u>የህገ መንግስት የበላይነት</u>

አንድ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት የህግ መንግስት የበላይነት አንቀጽ ሊኖራው ይገባል ተብሎ ህገ መንግስት አንድ ህብረተሰብ የሚመራበትን ስርዓት የሚነደፍበት ፖለቲከዊ መዋቅርና የህብረተሰቡ ዋና ዋና እስቶች የሚደነገጉበት በመሆኑ የህጎች ሁሉ ቁንጮ ተደርጎ ይወሰዳል።

ይህ ማለት ህገ መንግስት ከመንግስት አካላትም በላይ በመሆኑ የመንግት አካላት በህገ መንግስት ገደብ ስር ተግባራቸውን ማከናወን እንደላባቸው የሚያመለክት መርህ ነው
በአንድ ህገ መንግስት ውስጥ የህገ መንግስት የበላይነት ርዕሰ አንቀጽ ካለ ይህንን የህገ መንግስት የበላይነት የማስከበር ኃላፊነት ያለው አካል መኖር አለበት፡፡

ለምሳሌ በአሜሪካ ህገ መንግስት የህገ መንግስት የበላይነትን የሚደነግግ አንቀጽ የሚገኝ ሲሆን የህገ መንግስቱን የበላይነት የሚያስከብር አከል ደግሞ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት ህገ መንግስቱን የሚቃረን ኮንግረሱ የሚያወጣቸው ህጎች የመንግስት አካላት የሚወስኑአቸው ውሳኔዎች ወይም ማናቸውም ህገ መንግስቱን የሚያፋልሱ ተግባራትን የመሻር ስልጣን አለው፡፡
በተመሳሳይ ሁኔታ በህንድ ህገ መንግስት ውስጥም የህገ መንግስቱ የበላይነት ርዕስ አንቀጽ የተካተተ ሲሆን ህገ መንግስቱን የሚፃረር ማናቸውም ህግ ውሳኔዎችና ስራ ተፈጻሚነት እንደሌለው በህገ መንግስቱ ውስጥ ተደንግጓል፡፡

የህንድ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የህንድ ህገ መንግስት የሚጻረሩ ህጎች ውሳኔዎችና ስራዎች ተፈጻሚነት እንዳይኖራቸው የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በኤፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9(1) ህገ መንግስቱ የበላይ ህግ እንደሆነ ማንኛውም ህግ ልማዳዊ አሰራር የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ህገ መንግስቱን የሚቀረን ከሆነ ተፈጻሚነት እንደሌለው ተደንግጓል፡፡

ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9(2) ላይ ለመረዳት እንደሚቻለው የህገ መንግስቱን የበላይነት የማስከበር ስልጣን እላይ እንደተጠቀሱት አገሮች አሰራር ለአንድ አካል (ጠቅላይ ፍ/ቤት) የተሰጠ አይደለም፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ማንኛውም ዜጋ የመንግስት አካላት የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራትና ባለ ስልጠኖቻቸው ህገ መንግስቱን የማስከበርና ለህገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት እንደለባቸው ተገልጿል፡፡ እነዚህ አካላት ለህገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት የሚያጠያይቅ ነገር ባይሆንም የህገ መንግስቱን የበላይነት የማከበር ስልጣን በተመለከተ ይህ ስልጣን ለአንድ አካል ተለይቶ አለመሰጠቱ ኢተግባራዊነቱ ወይም ከአፈጻጸም አንፃር ጉዳዩን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

ሐ. <u>የመንግስት ስልጣን ክፍፍል</u>

የመንግስት መዋቅር የህገ መንግስት መሰረታዊ ይዘት ሲሆን መንግስት በምን አይነት ስርዓት መመስረት እንዳለበትም በህገ መንግስት ውስጥ ነው የሚደነገግ ሆኖ የመንግስት አካላት ስልጣን ክፍፍልም የሚደረገው በህገ መንግስት ነው፡፡

በዲሞክሲያዊ ህገ መንግስት ውስጥ የመንግስት ስልጣን ለሦስት የመንግስት አካል ተከፍሎ ይሰጣል፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መንግስት ማለት ህብረተሰቡን በመወከል ህግና ስርአትን በመደንገግ ህብረተሰቡን የሚያስተዳደር ሲሆን ስልጣኑም ህግ አውጭ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈጻሚ በመባል ለሦስቱ የመንግስት አካላት ይሰጣል፡፡

ሦስቱም የመንግስት አካላት የተለያዩ ተግባራት የሚኖራቸው ሲሆን አንዱ አካል ያአንዱን አካል ተግባር ማከናዋን የለበትም፡፡ አንዱ አካል በሌላው አካል ስራ ውስጥም ጠልቃ መግባት የለበትም፡፡ የሦስቱም አካል ተግባር ተጠቅልሎ ለአንዱ አካል መሰጠት የለበትም
ሚዛናዊ የመንግስት ስልጣን የሚኖረው የመንግስት ስልጣን ለሦስት ተከፍሎ እርስ በርሱ ለምጠባበቅ ሶስት የመንግስት ክፍል ሲሰጥ ነው የሚል እሳቤ የስልጣን ክፍፍሉ መሰረት ነው፡፡ የሦስቱ መንግስት አካላት ስልጣን መቀላቀል አንድ ላይ መሆን ወይም በአንድ አካል መያዝ አምባገነንነትን ወይም ፈላጭ ቆራጭነትን የሚያስከትል እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ በመሆኑ የመንግስት ስልጣን ክፍፍል ህገ መንግስታዊ መሰረት እንዲኖረው የሚደረገው፡፡ የአስተዳደር ህግም ሚዛናዊ የመንግስት ስልጣን እንዲሰፍን በማድረግ የዜጎችን መብት ማስከበር ላይ ያነጣጠረ ስለሆነ ህገ መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል እሳቤን የሚጋራ ነው፡፡

መ. <u>የዳኝነት ነፃነትና የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ የመከለስ ስልጣን</u>

የህግ የበላይነት ስርዓት ለማክበር ነፃ የሆነ የዳኝነት አካል አስፈላጊ ነው፡፡ ነፃ የሆነ የዳንኝነት አካል መኖር ትክክለኛ ያልሆነ የአስተዳደር አካላትን ስራዎች በመቆጣጠር የህግ የበላይነትን በማስከበር ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡

የአስተዳደር አካላት በውሳኔቸአው የግለሰቦችን መብት በሚጥሱበት ጊዜ ፍ/ቤቶች በአስተዳደሩ አካል ውሳኔ የተጣሰውን የግለሰቦች መብት ያስከብራሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ደግሞ የዳኝነቱ አከል የህገ መንግስት ጠባቂም ተደርጎ ይወሰደል፡፡ ይህ በመሆኑም የዳኝነቱ አካል ነፃ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ የዳኝነቱ አካል ነፃ ካልሆነ ህገ ወጥ የሆነ የአስተዳደር አካላትን ስራዎች በመቆጣጠር የግለሳቦችን መብት ማስከበር አይቻለውም፡፡ በዚህ ምክንያት የዳኝነት ነፃነትና የአስተዳደር ውሳኔዎችን የመከለስ የዳኝነት ስልጣን ህገ መንግስታዊ ቦታ እንዲኖረው ይደረገል፡፡ ይህ ህገ መንግስታዊ መሪህ ደግሞ የአስተዳደር ህግም መሰረታዊ ይዞታ ነው፡፡

1.4. <u>የአስተዳደር አካላትን ውሳኔዎች የመከለስ የፍ/ቤቶች ስልጣን በኢፌዲሪ ህገ መንግስት</u>

የአስተዳደር አካላትን ውሳኔዎች የመከለስ የፍ/ቤቶች ስልጣን በአገራችን የህግ ስርዓት ውስጥ ህገ መንግስታዊ መሰረት ያለው መርህ ነው፡፡
ከዚህ በላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የኢፌዴሪ ህገ መንግስት ዓለማ በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረት አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መመስረት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በህግ የበላይነት ስርዓት ውስጥ ደግሞ የሰው መብትና ግዴታ የሚወሰነው በዳኝነቱ አካል ነው፡፡
በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78(1) ስር እንደተመለከተው በአገራችን ነፃ የሆነ የዳኝነት አካል ተቋቁሟል፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 79(1) ስር ደግሞ የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ የዳኝነት ስልጣን ማለት ደግሞ በመብት ክርክር ላይ የመወሰን ስልጣን ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የአስተዳደሩ አካል ውሳኔ የግለሰቦችን መብት የሚነካ ሆኖ ክርክር ካስነሳ ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የመወሰን ህገ መንግስታዊ ስልጣን ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

ሌላው ለዳኝነቱ አካል የአስተዳደር አካላቱን ውሳኔ የመከለስ ስልጣን የሚሰጠው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ማንኛውም በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ያለው ሰው ጉዳዩን ለደኝነት አካል በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት እንደለው ያመለክታል፡፡ ለግለሰቦች በፍርድ ሊወሰን የሚገባን ጉዳይ ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብት የሚሰጠው ድንጋጌ በአንፃሩ ለፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የመወሰን ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ

ጉዳይ በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ምክንያት የሚፈጠረውን የመብት ክርክርም የሚያጠቃልል ነው፡፡

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ ለፍ/ቤቶች ቀርቦ ውሳኔ የሚያገኘው ጉዳይ ማንኛውም ጉዳይ ሁሉ ሳይሆን በፍርድ ሊወሰን የሚገባ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ምን አይነት ጉዳይ እንደሆነ በህገ መንግስቱ ላይ አልተመለከተም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የተፃፉ ጽሑፎች በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ትርጉም ከማስቀመጥ ይልቅ በፍርድ ሊወሰኑ የማይችሉትን ጉዳዮች በመዘርዘር ከዝርዝሩ ውጭ የሆኑ ጉዳዮች በፍርድ የሚወሰኑ ጉዳዮች እንደሆኑ ያስቀምጣሉ፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ጉዳዮች የፖሊስ ውሳኔዎች የግለሰቦች ጥቅም የላለባቸው ጉዳዮች በፍርድ የማይወሰኑ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ብቻ እንደሆኑ በመወሰድ ከዚህ ውጭ የሆኑ ማናቸውም የመብት ጥያቄዎች በፍርድ የሚወሰኑ ጉዳዮች እንደሆኑ ይወስደሉ፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የአስተዳደር ሕግ ምን አይነት ሕግ ነው?
2. በሕገመንግስት የተረጋገጡ የዜጎች መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነትን ከማረጋገጥ አንጻር የአስተዳደር ሕግ ሚና ምንድነው?

<u>ክፍል ሁለት</u>

2. <u>የአስተዳደር ውሳኔዎችን በዳኝነት አካል የመከለስ</u> (Judcial Review)

<u>አጠቃላይ መርሆዎች</u>

የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል ተከታትለው ሲያጠናቅቁ፡-

- **የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በዳኝነት አካላት ለመከለስ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን ይለያሉ፤**
- **የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በዳኝነት አካላት የሚከለስበትን መስፈርት በተመለከተ የተወሰኑ አገራትን ተሞክሮ ያውቃሉ፤**
- **የአስተዳደር ውሳኔዎችን በፍርድ ቤት የመከለስ ስልጣን አጠቃላይ መርሆዎችን በመለየት ለተግባራዊነቱ ይሰራሉ፡፡**

ከላይ በክፍለትምህርቱ መግቢያ ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የአስተዳደር አካላት ባቋቋማቸው ሕጎች የተቋቋሙለትን ዓላማ ገቢራዊ ለማድረግ በተሰጣቸው የስልጣን ክልል ውስጥ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአስተዳደር አካላት በተለይ እንደሁኔታው ስራ ላይ የሚያውሉትን ስልጣን (Discretionary power) **በሚጠቀሙበት ወቅት ከስልጣናቸው ውጭ ወጥተዋል/አልወጡም የሚለውን መወሰኑ አስቸጋሪ ቢሆንም እራሳቸው ያስተዳደር አካላቱ በሚያወጧቸው መመሪያዎች ይህንን ሰፊ ስልጣን መገደቡ በተለያዩ የህግ ስርዓቶች የተለመደ ነው፡፡**

የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በዳኝነት አካላት ስለሚከለሱበት አግባብ ስንነጋገር ሁለት ሁኔታዎችን ለይተን ማጤን ይገባል፡፡

- **አንደኛው የአስተዳደር አካላት እንደጉዳዩ ምክንያታዊ ነው በሚሉት ሁኔታ ለመደሰን በተሰጣቸው ስልጣን**(Discretionary power) **ተጠቅመው ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት ሊከተሉት የሚገባ ዝርዝር ስነስርዓት (የባለጉዳዩን የመሰማት መብት ማክበር እንዳለባቸው፣ ለሚሰጡት ውሳኔ ምክንያት መስጠት እንዳለባቸው ወዘተ) የአስተዳደር አካላቱን ባቋቋሙ ወይም በሌሎች ሕጎች ተዘርዝረው በሚገኙ ጊዜ ያለውን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ በዚህ ጊዜ የአስተዳደር አካላቱ በሰጡት ውሳኔ ላይ የቀረበን ቅሬታ የሚያዩ የዳኝነት**

አካላት የአስተዳደር አካላቱ በሕግ ተዘርዝሮ የተቀመጠውን ስነስርዓት ሳይከተሉ ውሳኔ መስጠታቸውን ካረጋገጡ ውሳኔውን ውድቅ በማድረግ ጉዳዩ ስነስርዓቱን ተከትሎ እንዲታይ ወደ አስተዳደር አካላቱ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡(በይግባኝ ባይ ዳምጠው ጉድሬ ጉዳይ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ክፍል 3 ስር የተጠቀሰውን ከጥብቅና ፈቃድ ስረዛ ጋር የተያያዘ ውሳኔ እዚህ ቦታ በምሳሌነት ሊነሳ ይችላል፡፡)

- ሁለተኛው ደግሞ የአስተዳደር አካላት እንደጉዳዩ ምክንያታዊ ነው በሚሉት ሁኔታ ለመወሰን በተሰጣቸው ስልጣን(Discretionary power) መሰረት ስለሚሰጡት ውሳኔ አሰጣጥ በዝርዝር የተቀመጠ ስነስርዓት በሌለበት ሁኔታ በተሰጠ ውሳኔ ላይ የሚቀርብን ቅሬታ የዳኝነት አካላት በድጋሚ የሚያዩበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ በዚህ ጊዜ የዳኝነት አካላት ወደ ውሳኔው ስረነገር (merit) ምርመራ ወይም የፖሊሲ ምርጫ በማካሄድ በሶስቱ የመንግስት አካላት መካከል የተደረገውን የስልጣን ክፍፍል ወደመንካት እንዳይገቡ ጥንቃቄ በማድረግ በተሰጡት ውሳኔዎች ሕጋዊነት (የአስተዳደር አካላት ከተቋቋሙበት ሕግ አላማ ውጭ ስልጣናቸውን አላግባብ ስላለመጠቀማቸው ወዘተ) ላይ በማትኮር ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሚቀጥለው ክፍል ስር እንደምናየው የዳኝነት አካላት በአስተዳደር አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎችን የሚከልሱበት ሁኔታ በአገራችን በተለያዩ ሕጎች ስር የሚገኙ እና በተወሰነ ደረጃ ደግሞ በዳኞች በአሰራር በዳበሩ መርሆዎች ላይ የተመሰረቱ በመሆኑ በፍርድ ቤቶች የተለያዩ አሰራሮች ይስተዋላሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ የሚከልሱበትን አንድወጥ አሰራር ያካተተ የአስተዳደር ስነስርዓት ሕግ እስኪወጣ ድረስ የተሻለ ተገማችነት ያለው ውሳኔ ላይ ለመድረስ የራሱ አስተዋጽዖ ሊኖረው ይችላል በሚል እምነት የተወሰኑ አገራትን ተሞክሮ ለማየት እንሞክራለን፡፡

በዚሁ መሰረት በተለያዩ አይነት አደረጃጀቶች የሚደረጉ ክለሳዎችን ለማየት እንዲረዳ ጭምር ታስቦ በአስተዳደር ህግ የተሻለ ተሞክሮ አላቸው ተብለው በተመረጡት በፈረንሳይ፣ በኔዘርላንድ እና በዩናይትድ ኪንግደም የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በህግ መሰረት መሰጠታቸውንና የዜጎችን መብት አለመጣሳቸውን ለማረጋገጥ

በዳኝነት አካላት በምን ዓይነት መርሆዎች ላይ ተመስርተው እንደሚከለሱ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

2.1 ከመደበኛ የዳኝነት አካላት ውጭ በሚገኝ እራሱን በቻለ የአስተዳደር ፍርድ ቤት የሚከለስበት ሁኔታ

በዚህ ዓይነት አሰራር በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀሰው በአስተዳደር ሕግ የዳበረ የሕግ ተሞክሮ አላቸው ከሚባሉ አገሮች አንዷና የአህጉራዊ ሕግ ስርዓት (Continental Legal System) አካል የሆነችው ፈረንሳይ ነች፡፡ የአስተዳደር አካላት የተሰጣቸውን ስልጣን በስራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት ከሕግ ውጭ እንዳይሰሩ እና የዜጎችን መብት እንዳይጥሱ ለመቆጣጠር ፈረንሳይ ከመደበኛ የዳኝነት አካላት ውጭ የሆኑ እራሳቸውን ችለው የተዋቀሩ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶችን በማደራጀት ትታወቃለች፡፡

በዚህ ስርዓት የአስተዳደር አካላት በሰጧቸው ውሳኔዎች መብቱ ተነክቷል የሚሉ ሰዎች በቅድሚያ በአስተዳደር አካላቱ ውስጥ ያሉትን መፍትሄዎች ካሟጠጡ በኋላ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቶች አቤቱታቸውን የማቅረብ ዕድል አላቸው፡፡

በፈረንሳይ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ሦስት ደረጃ (Layers) አሏቸው፡፡ እነርሱም፡-

(I) የአስተዳደር ትሪቡናልስ (*Tribunaux Administratifs*)

(II) የአስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች (Court Administrative d'appel)

(III) ኮንሴ ዴታ (Conseil d'Etat)

በመባል ይታወቃሉ፡፡

በአስተዳደር አካላት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመጀመሪያ የሚያዩት የአስተዳደር ትሪቡናልስ ናቸው፡፡ የአስተዳደር ትሪቡናልስ በሰጧቸው ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች አቤቱታቸውን ለአስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ ይችላሉ፡፡ የአስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ በአስተዳደር ትሪቡናልስ የተሰጡ ውሳኔዎችን ሙሉ ለሙሉ እንደገና በማየት መዳኘት ስልጣን አላቸው፡፡

የአስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በሚሠጡት ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በአስተዳደር ፍርድ ቤቶቹ እርከን የመጨረሻ/ከፍተኛ ወደ ሆነው ኮንሴዬታ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡ ይህ በፈረንሳይ በአስተዳደር ጉዳይ የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው የአስተዳደር ዳኝነት አካል በይግባኝ ሰሚ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ በድጋሚ ወደማየት ሳይገባ ቅሬታ የቀረበበትን ውሳኔ የሚመረምርባቸውን አጠቃላይ መስፈርቶች/መርሆዎች(Unwritten General Principles of Law) ከረጅም ጊዜ ልምዱ በመነሳት አዳብሯል፡፡ ከነዚህም መርሆዎች ውስጥ ፡-

- በተለይ በግብር አጣጣል፣ በሕዝብ ሃብት የመጠቀም ወዘተ የእኩልነት መርህ (Principle of Equality)፣
- በአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የስነ ስርዓት ደንቦች (Procedural Rules) መከበራቸውን እና ሕግ በትክክል የተተረጎመ መሆኑን የሚጣራበት መርህ፣ እና
- በተለይ በአስተዳደር ውሳኔ መብታቸው የሚነካ ግለሰቦች ጥቅም ከአንድ ንብረት ለሕዝብ ጥቅም መወረስ ጋር የሚመዘንበት የአስተዳደር ውሳኔ ተመጣጣኝነት (Proportionality)

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለማየት ከሞከርነው የፈረንሳይ የአስተዳደር ሕግ ከመደበኛ የዳኝነት ስርዓት ውጭ ራሳቸውን ችለውና ብቸኛ ስልጣን ኖሯቸው በአስተዳደሩ ውስጥ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ መጨረሻው ድረስ የአስተዳደር አካላት ተግባራት ሕጋዊነት የሚፈተሽ መሆኑን እንዲሁም በአስተዳደር ጉዳይ የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ያለው ኮንሴዬታ በአስተዳደር ጉዳይ የተሰጠን ውሳኔ ለመከለስ ውሳኔ ሰጪው አካል ሕግን በአግባቡ ስለመተርጎሙ፣የስነስርዓት ድንጋጌዎችን በአግባቡ መከተሉን እና የዜጎች የእኩልነት መብት አለመገፋቱ ወዘተ የሚጣሩበት አጠቃላይ መርሆዎች በማዳበር የአስተዳደር አካላት በህግ ከተሰጣቸው ስልጣን ክልል ውጭ ሳይወጡ መስራታቸው የሚረጋገጥበት ስርዓት መዘርጋቱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

2.2 በመደበኛ የዳኝነት አካል ውስጥ በሚገኝ የአስተዳደር ጉዳይ ልዩ ችሎት ክለሳ ስለሚደረግበት ሁኔታ

የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በመደበኛ የዳኝነት አካል ውስጥ በሚገኝ የአስተዳደር ሕግ ችሎት ከሚታይባቸው አገራት ውስጥ የኔዘርላንድን ልምድ እናያለን፡፡ የአስተዳደር አካላት ከሚሰጡት ውሳኔ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎች የሚታዩበትን መስፈርቶች የሚመለከቱ መርሆዎችን ያካተተ አጠቃላይ የአስተዳደር ሕግ (General Administrative Law Act/*Algemene Wet Bestuursrecht*) እ.ኤ.አ በ1994 ኔዘርላንድ አውጥታለች፡፡

በኔዘርላንድ አጠቃላይ የአስተዳደር ሕግ መሰረት በአስተዳደር አካላት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች በቅድሚያ በአስተዳደር አካላቱ ውስጥ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ጉዳያቸው በአስተዳደር አካሉ በድጋሚ እንዲታይ የመቃወሚያ ማስታወቂያ ስነስርዓትን (Notice of Objection Procedure) ከተጠቀሙ በኋላ በዚህ ደረጃ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በመደበኛ የአካባቢ ፍርድ ቤት (District Court) ውስጥ የአስተዳደር ጉዳዮችን የሚያይ የተለየ የአስተዳደር ችሎት (Administrative Law Division) ተደራጅቷል፡፡

የአስተዳደር ሕግ ችሎቶች በአስተዳደር አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎችን በሚከልሱበት ወቅት በመስፈርትነት የሚጠቀሙባቸው የስነስርዓት መርሆዎች (Procedural norms) እና የፍሬ ነገር መርሆዎች (Substantive norms) በኔዘርላንድ አጠቃላይ የአስተዳደር ሕግ ውስጥ በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡

የስነ ስርዓት መርሆዎች ከሚባሉት ውስጥ፡-

- የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት አግባብነት ያላቸውን አስፈላጊ መረጃዎች የመሰብሰብ እና የተለያዩ ጥቅሞችን (Interests) ማመዛዘን እንዳለባቸው የሚያመለክተው ጥንቃቄ የማድረግ መርህ (The Duty to Care Principle) እና

- የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት ለውሳኔያቸው ምክንያት መስጠት እንደሚገባቸው የሚያመለክተው መርህ(The Duty to give Reasons)

ይገኙበታል።

የፍሬ ነገር መርሆዎች ከሚባሉት ውስጥ ደግሞ ፡-

- የአስተዳደር አካላት በሕግ የተሰጣቸውን ስልጣን ከታሰበው አላማ ውጭ ለሆነ ተግባር አለመጠቀማቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳው ስልጣንን አላግባብ እንዳይጠቀሙ የሚከለክለው መርህ (Prohibition against Abuse of Power)፣
- የአስተዳደር አካላት በሚሰጡት ትዕዛዝ የሚገኘውን ጥቅም በዚህ ትእዛዝ መብቱ ከሚጎዳ ሰው ጥቅም ጋር ተመዛዝኖ ተገቢው እንዲፈጸም ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚያስገድደው የተመጣጣኝነት መርህ (Principle of Proportionality)፣
- የአስተዳደር አካላት ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን በእኩል ሁኔታ እንዲያዩ፤ እነዲሁም የተለያዩ ጉዳዮችን ደግሞ በተለያየ ሁኔታ እንዲያዩ የሚያስገድደው የእኩልነት መርህ (Principle of Equality) እና
- የአስተዳደር አካላት ባልተጠበቀ ሁኔታ ፖሊሲያቸውን በመቀየር ዜጎች በጉልህ በሚታይ ሁኔታ እንዳይጎዱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ የሚያስቀምጠው የሕግ እርግጠኝነት መርህ(Principle of Legal Certainty)

የሚሉት ይገኙበታል።

ከላይ ባጭሩ ለመዳሰስ ከሞከርነው በኔዘርላንድ የአስተዳደር አካለት ውሳኔ በአካባቢ ፍርድ ቤቶች ውስጥ በሚገኝ የአስተዳደር ሕግ ችሎት እንደሚከለስ እና ለዚህ ተግባር የሚያገለግሉ መስፈርቶች በሕግ ተዘርዝረው የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን ለመረዳት ይቻላል።

2.3 <u>በመደበኛ የዳኝነት አካል የአስተዳደር ውሳኔ ክለሳ ስለሚደረግበት ሁኔታ</u>

የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በዚህ ዓይነት ስርዓት ቁጥጥር ከሚያደርጉ አገሮች ውስጥ የአንግሎ አሜሪካን የሕግ ስርዓት አካል የሆነችውን ዩናይትድ ኪንግደምን በምሳሌነት እናያለን፡፡ የአስተዳደር አካላት በሕግ ከተሰጣቸው ስልጣን ክልል ውጭ ወጥተው የግለሰቦችን መብት የሚጋፋ ውሳኔ እንዳይሰጡ ወይም በስልጣን ክልላቸው ውስጥ ብቻ የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ በዩናይትድ ኪንግደም በተለያዩ ትሪቡናልስ፣በፓርላማ ኮሚሽነሮች/እንባጠባቂዎች (Parliamentary Commissionor/Ombudsmen) እንዲሁም በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚደረግ የአስተዳደር ውሳኔ ክለሳ የዳበረ አሰራር ነው፡፡

የአስተዳደር ትሪቡናልስ የአስተዳደር አካላት የሰጧቸውን ውሳኔዎች ፍሬ ነገር (Substance and merit) ጭምር በመመርመር ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ የአስተዳደር ትሪቡናልስ ለሚሰጡት ውሳኔ ምክንያት መስጠት እንዳለባቸው እ.ኤ.አ በ1992 በወጣው Tribunals and Inquiries Act ክፍል 10 ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

በአስተዳደር አካላት እና በአስተዳደር ትሪቡናልስ የሚሰጡ ውሳኔዎች የዜጎች መብት እንዳይጣስ በመጠበቅ በዩናይትድ ኪንግደም ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኙ የዜጎችን ከበሬታ ያገኙ ተቋማት ናቸው፡፡ የመደበኛ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ የመከለስ ስልጣን የውሳኔውን ሕጋዊነት (Legality)፣ ወይም ሕገወጥነት(Illegality/Unlawfulness)፣ ኢምክንያታዊነት (Irrationality/unreasonableness) እና ስነ ስርዓታዊ ግድፈት (Procedural Impropriety/Unfairness) በሚፈትሹ ወዘተ ፍርድ ቤቶቹ ባዳበሯቸው መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህ ስርዓት መደበኛ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላት ወደሰጡት ውሳኔ ስረነገር (Merit) ሳይገቡ ከሚቀርቡላቸው ጉዳዮች በመነሳት ባዳበሯቸው ዳኛ ሰራሽ መርሆዎች ላይ በመመስረት ባጠቃላይ ስለውሳኔዎቹ ሕጋዊነት፣ በሕግ በተቀመጠ ስነስርዓት መሰረት መሰጠቱን ወዘተ በመፈተሽ የአስተዳደር አካላቱን ውሳኔዎች በመከለስ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡

የአስተዳደር አካላት በሕግ የተቀመጡ ዝርዝር የስነ ስርዓት ድንጋጌዎችን ወይም ዳኛ ሰራሽ ሕጎችን በመተላለፍ ውሳኔ ሰጥተው ከተገኙ ቅሬታ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ የስነ ስርዓት ግድፈት (Procedural Ultra Virus) እንዳለበት በመውሰድ ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደርጉታል።

የዩናይትድ ኪንግደም መደበኛ ፍርድ ቤቶች ከላይ በተጠቀሱት መስፈርቶች ተጠቅመው የአስተዳደር አካላትን ወይም የአስተዳደር ትሪቡናሎችን ውሳኔ በሚከልሱበት ወቅት በረጅም ሂደት ባዳበሯቸው በመመርመር ግድፈት እንዳለበት ከደረሱበት ውሳኔውን ውድቅ የሚያደርግ ትዕዛዝ (Quashing Order /*certiorari*/)፣ የተፈጥሮ ሕግን ከመተላለፍ እንዲቆጠብ ወይም ከስልጣኑ መተላለፉን እንዲያቆም (Prohibition Order) እና የአስተዳደር አካሉ አንድ ሕዝባዊ ግዴታ (Public duty) እንዲወጣ ለማዘዝ (Mandatory Order /*mandamus*/) ይችላሉ።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በመከለስ ሂደት የዳኝነት አካላት ከስልጣን ክልላቸው በመውጣት በአስተዳደሩ አካል ስራ አላግባብ እንዳይገቡ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል?
2. በዚህ ክፍል ካየናቸው ሶስት አገሮች ተሞክሮ በመነሳት የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ለመከለስ በመስፈርትነት ቢወሰዱ በአገራችን የሕግ ስርዓት ተቀባይነት ያላቸው/ሊኖራቸው ይገባል የሚሏቸው የትኞቹ መስፈርቶች/መርሆዎች ናቸው? ምክንያትዎን በመስጠት ያብራሩ።

ክፍል ሶስት

3. **የአስተዳደር አካላትን ውሳኔዎች የመከለስ የፍርድ ቤቶች ስልጣን እና በአገራችን ስላለው አፈጻጸም**

የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል ተከታትለው ሲያጠናቅቁ፡-

- በአገራችን ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላት ውሳኔ የመከለስ ስልጣን ለይተው ያውቃሉ፣
- በአገራችን የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በዳኝነት አካላት የሚከለስበትን ሁኔታ በተመለከተ የተወሰኑ አዋጆችን ይለያሉ፣
- የአስተዳደር ውሳኔን በዳኝነት አካላት መከለስን በተመለከተ የተሻሉ አሰራሮችን በመለየት ለተግባራዊነቱ ይሰራሉ፡፡

ቀደም ሲል በነበረው የዚህ ክፍለትምህርት ክፍል ለመግለጽ እንደተሞከረው በአገራችን አንድ ወጥ የስተዳደር ስነስርዓት ሕግ ባለመኖሩ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በዳኝነት አካላት በሚከለስበት ሁኔታ ላይ አንድ ወጥ አሰራር አለ ለማለት እንደማይቻል መገለጹ ይታወሳል፡፡ ይህ ሁኔታ ሊፈጠር ከቻለባቸው ምክንያቶች ውስጥ የአስተዳደር አካላቱን በማቋቋም ስልጣናቸውን የሚዘረዝሩ አዋጆች የአስተዳደር አካላቱ እንደሁኔታው በስራቸው ሂደት በሚሰጧቸው ውሳኔዎች ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ በተለያየ ሁኔታ ማስቀመጣቸው በዋነኛነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ይህም ማለት የተወሰኑት ማቋቋሚያ አዋጆች በአስተዳደር አካላቱ ውሳኔ ያልተስማማ ሰው በደፈናው ለዳኝነት አካላት ቅሬታውን ለማቅረብ እንደሚችል የሚጠቁሙ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ ቅሬታ ለዳኝነት አካል መቅረብ እንደሚችል አስቀምጠዋል፡፡ ከተጠቀሱት በተለየ ሁኔታ የአስተዳደር አካላት የሰጡት ውሳኔ የመጨረሻ እንደሆነ በመውሰድ ለሌላ አካል ቅሬታ ማቅረብ እንደማይቻል የደነገጉ እንዲሁም በአስተዳደር አካላቱ ውሳኔ ላይ ለሌላ አካል(የዳኝነት አካላትን ጨምሮ) ቅሬታ ማቅረብ ስለመቻል/አለመቻሉ በዝምታ ያለፉ አዋጆችም ይገኛሉ፡፡

በዚህ ክፍል የአስተዳደር አካላቱን ውሳኔ የመከለስ ስልጣን ለዳኝነት አካል በግልጽ በተሰጠበት ሁኔታ እና ይህ ስልጣን በግልጽ ባልተሰጠበት ሁኔታ የዳኝነት አካላት የመከለስ ጥያቄን ሊያስተናግዱ የሚችሉበትን ሁኔታ ተራ በተራ እንደሚከተለው እናያለን፡፡

3.1 <u>የመከለስ ስልጣን ለፍርድ ቤቶች በሕግ በግልጽ የተሰጠባቸው ሁኔታዎች</u>

የአስተዳደር አካላት በህግ የተሰጣቸውን ስልጣን ስራ ላይ በሚያውሉበት ወቅት በህግ በታሰበው መሰረት የሚያስፈጽሙትን ሕግ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ እና በስራቸው ሂደትም ህግን በመተላለፍ የዜጎችን መብት አለመጋፋታቸው ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች አንዱ እነዚህ አካላት የሚሰጡት ውሳኔ ላይ የዳኝነት አካላት በተወሰነ ደረጃ ቁጥጥር የሚያደርጉበትን ስርዓት በማመቻቸት ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሰረት በአገራችን ሕግ አውጪ አካላት የወጡ የተወሰኑ ሕጎች የአስተዳደር አካላት በሰጧቸው ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለዳኝነት አካላት ማቅረብ እንደሚቻል በግልጽ አስቀምጠው እናገኛለን፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሰጠው የመድን ስራ ፈቃድ ስረዛ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው አቤቱታውን ለማዕከላዊ (ለአሁኑ ፌደራል) ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል (የመድን ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 86/1986 አንቀጽ 7(2) &(3))፣

- ከምርጫ ጋር በተያያዘ በመራጮች ምዝገባ ሂደት በሚነሱ አለመግባባቶች የወረዳው የምርጫ ጽ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ለወረዳ ፍርድ ቤት፤ በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት በተነሱ አለመግባባቶች በዞኑ ወይም በክልል ምርጫ ጽ/ቤት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤በድምጽ አሰጣጥ ሂደት በተነሱ አለመግባባቶች የወረዳው ምርጫ ጽ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለወረዳ ፍርድ ቤት፤በቆጠራ ሂደት በሚነሱ አቤቱታዎች ላይ ደግሞ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለማዕከላዊ (ለአሁኑ ፌደራል) ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል (የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅን ከኢፌዲሪ ሕገመንግስት ጋር ለማጣጣም የወጣ አዋጅ ቁጥር 111/1987 አንቀጽ 69(4)፣ 70(4)፣ 71(4) እና 72(4))፣

- የግብር ይግባኝ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የጉባኤው ውሳኔ በተሰጠ 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ ስለህጉ ስህተት ፍርድ ሊጠይቅ እንደሚችል (የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 112(1))፣

- ከጥብቅና ፈቃድ ጋር በተያያዘ በፍትህ ሚኒስትሩ የተሰጠ ውሳኔ የህግ ስሕተት አለበት የሚል ቅሬታ ያለው ወገን ውሳኔው በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል (የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 29(1))፣

- በመንግስት ሰራተኞች ጉዳይ የአስተዳደር ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለ የሚል ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል (የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 76(2))፣እና

- ኢትዮጵያዊ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት(Charity) ወይም ማሕበር (Society) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው የቦርዱ ውሳኔ በተሰጠ 15 ቀን ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 104(3))፣

የሚሉት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በተጠቀሱትና በሌሎች ተመሳሳይ አዋጆች የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች “ይግባኝ” እንደሚቀርብ የተቀመጠው ከመደበኛ ይግባኝ በተለየ ሁኔታ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላት የተሻለ ሊረዱት እና ውሳኔ እንዲሰጡበት ወደታሰበ ጉዳይ ስረነገር ሳይገቡ ባጠቃላይ ቅሬታ

በቀረበበት ውሳኔ ሕጋዊነት ላይ ትኩረት በማድረግ መወሰን እንደሚጠበቅባቸው መረዳቱ የተሻለ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በተጠቀሱት አይነት አዋጆች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የዳኝነት አካላት ወደሚያስተናግዱበት ሁኔታ ስንመጣ በቅድሚያ መታየት ያለበት ቅሬታ አቅራቢዎቹ በመጀመሪያ በአስተዳደር አካላቱ ውስጥ የተዘረጉ ቅሬታ የሚቀርብባቸውን መድረኮች አሟጠው የተጠቀሙ (Exhaust ያደረጉ) መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ቅሬታ ያላቸው ሰዎች ያለብዙ ድካም እና ወጪ መፍትሄ በማግኘት ጉዳያቸው በአጭሩ እንዲቋጭ ከማድረጉም በላይ የዳኝነት አካሉም አላስፈላጊ ለሆነ የስራ ጫና እንዳይዳረጉ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

የዳኝነት አካላት በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን በመጠቀም የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች ሕጋዊነት በመመርመር በርካታ ውሳኔዎች እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ከያዝነው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የዳኝነት አካላት ከሰጧቸው ውሳኔዎች ውስጥ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር የፍ/ይ/መ/ቁ.1965/92 በይግባኝ ባይ አቶ ዳምጠው ጉድሬ እና በመልስ ሰጪ የፍትህ ሚኒስቴር መካከል በነበረው ክርክር የሰጠው ውሳኔ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ይግባኙ ለፍርድ ቤት የቀረበው የፍትህ ሚኒስቴር በፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይግባኝ ባይ ፈቃድ ከማውጣታቸው በፊት የስነ ምግባር ችግር እንደነበረባቸው በመጥቀስ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የጻፈውን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል ለይግባኝ ባይ የሰጠውን የጥብቅና ፈቃድ መጋቢት 15 ቀን 1992 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በመሰረዙ ነው፡፡ ይግባኝ ባይ የጥብቅና ፈቃድ ለማውጣት ሲያመለክቱ በዳኝነት ያገለግሉበት ከነበረው የኦሮምያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ መሸኛና የስነምግባር ምስክርነት ያቀረቡ ቢሆንም የፍትህ ሚኒስቴር ከኦሮሚያ ምክር ቤት የተጻፈለትን ደብዳቤ በመቀበል የጥብቅና ፈቃዱ ሲወጣ የቀረበው ሕገወጥ ማስረጃ እንደነበር በመግለጽ የስረዛ እርምጃውን ወስዷል፡፡ ይግባኝ ባይ ጉዳያቸው በአዋጁ መሰረት ለጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባኤ ሳይቀርብ የጥብቅና ፈቃዳቸው እንዲሰረዝ በመልስ ሰጪ የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስሕተት እንዳለበት በመግለጽ እንዲታረም ለፍርድ ቤት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

መልስ ሰጪ የአመልካች የጥብቅና ፈቃድ የተሰረዘው ፈቃዱን ከማውጣታቸው በፊት በተፈጸመ ድርጊት በመሆኑ የጥብቅና ፈቃድ ከወጣ በኋላ የተፈጸመ የዲሲፕሊን ጉዳዮችን አይቶ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ የማቅረብ ኃላፊነት ላለው የዲሲፕሊን ጉባኤ የይግባኝ ባይ ጉዳይ የሚቀርብበት ምክንያት እንደሌለ እና የወሰደው እርምጃ ተገቢ እንደሆነ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 29 ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት መልስ ሰጪ በሰጠው ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ከተገኘ የማረም ስልጣን የተሰጠው ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሲመረምር ከቆየ በኋላ በ21/06/93 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤

> የፍትህ ሚኒስቴር ለይግባኝ ባይ የሰጠውን የጥብቅና ፈቃድ የሰረዘው ቢሆንም ከአዋጅ ቁጥር 199/92 አካያ ስረዛው ስነስርዓቱን ተከትሎ የተከናወነ ሆኖ አናገኘውም፡፡ በይግባኝ ባይ ላይ የቀረበው ክስ ለዲሲፕሊን ጉባኤው ቀርቦ አልታየም ጉባኤውም የይግባኝ ባዩን ክርክር ተቀብሎ አልመረመረም፡፡ ከዚህ አኳያ የፍትህ ሚኒስቴር በይግባኝ ባይ ላይ የወሰደው እርምጃ የህግ ስሕተት ነው፡፡

በማለት የጥብቅና ፈቃድ ስረዛውን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በመቀጠልም በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መልስ ሰጪ የይግባኝ ባይ ፈቃድ የተሰጠው የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ አቅርበው ነው የሚል ከሆነ ይህንኑ ክስ አዋጁ ባስቀመጠው ስነስርዓት መሰረት በጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባዔ አማካኝነት አይቶ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በአዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀጽ 29(2) መሰረት ፍርድ ቤቱ ለመልስ ሰጪ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ (በአዋጁ መሰረት ዲሲፕሊን ጉባኤ ፊት በይግባኝ ባይ ላይ የቀረበ ክስ ባለመኖሩ ወደስራቸው የተመለሱ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡)

ይህ ውሳኔ የተወሰነ ህግ የማስፈጸም ስልጣን የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላት ሕግ አውጪው አካል የዜጎችን መብት በተሻለ ሁኔታ ለማስከበር እና ፍትሀዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲረዱ በሚል ምክንያት ያስቀመጣቸውን የስነስርዓት መርሆዎች(ከላይ በተጠቀሰው ጉዳይ የመሰማት መብት) ተላልፈው የሚሰጡት ውሳኔ ምን ያህል የዜጎች

የመስራት መብት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ እንደሚችል ነው። በተጨማሪም የዳኝነት አካላት ወደዝርዝር የፍሬ ነገር ወዘተ ጉዳይ ሳይገቡ አስተዳደር አካል ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ሕጋዊነት (በሕግ በተቀመጠው ስነ ስርዓት መሰረት መሰጠቱን ወዘተ) በማየት እና ከህግ ውጭ ሆኖ ከተገኘ ውድቅ በማድረግ የዜጎችን መብት በማስከበር ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ለመረዳት ይቻላል።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በዚህ ክፍል በምሳልነት በቀረበው በይግባኝ ባይ ዳምጠው ጉድሬ እና መልስ ሰጪ በሆነው ፍትህ ሚኒስቴር ጉዳይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠው ውሳኔ ይስማማሉ? ለምን?
2. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የአስተዳደር አካል ውሳኔን ለመከለስ በመስፈርትነት የተጠቀመው ምነድነው? ይህ መስፈርት ከላይ በክፍል ሁለት ስር ልምዳቸውን ባየነው አገሮች ውስጥ ምን ያህል በጥቅም ላይ ውሏል? ይወያዩበት።
3. በአስተዳደር አካል በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚደረግ ክለሳ (Judicial Review) ከመደበኛ ይግባኝ የሚለይበት ሁኔታ አለ? ይወያዩበት።

3.2 <u>የመከለስ ስልጣን ለፍርድ ቤቶች በሕግ በግልጽ ባልተሰጠ ጊዜ ስላለ ሁኔታ</u>

የአስተዳደር አካላትን በማቋቋም የተወሰኑ የመንግስት ተግባራትን እንዲያስፈጽሙ ስልጣን የሚሰጡ የተወሰኑ አዋጆች በአስተዳደር አካላት በሚሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ስለሚቀርብበት ሁኔታ ሳይናገሩ በዝምታ አልፈው እናገኛለን። በቅርብ ጊዜ የወጣው የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 555/2000 እዚህ ቦታ በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ አይነት አዋጆች ስር የአስተዳደር

አካላቱ የሚሰጡትን ውሳኔ ሕጋዊነት ለማረጋገጥ የዳኝነት አካላት የመከለስ ሥልጣን አላቸው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል?

በአገራችን የሚገኙ የተወሰኑ ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሳኔ ለመረዳት እንደሚቻለው በተጠቀሱት ሁኔታዎች ፍርድ ቤቶች የሚይዙት አቋም የተለያየ ሆኖ እናገኛለን፡፡ እነኚህን አቋሞች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎችን መሰረት በማድረግ እነደሚከተለው እናያለን፡፡

- አንዳንድ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን ውሳኔ የመከለስ ስልጣን እንዳላቸው በግልጽ ካልተቀመጠ ቅሬታዎችን ከማስተናገድ ሲቆጠቡ ይታያል፡፡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 9/87/25/ የተሰጠው ውሳኔ እዚህ ቦታ መጥቀሱ አግባብነት ይኖረዋል፡፡ በዚህ የምስራቅ ኦሮሚያ አንድነት የጫት ላኪዎች አክሲዮን ማህበር በይግባኝ ባይነት የንግድ ሚኒስቴር ደግሞ በመልስ ሰጪነት በቀረቡበት ጉዳይ ይግባኝ ባይ አላግባብ በመልስ ሰጪ የንግድ ፈቃዱ መታገዱን በመቃወም ዕገዳው እንዲነሳ ፍርድ ቤቱን ጠይቋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ሲመረምር ከቆየ በኋላ ጥቅምት 8 ቀን 1993 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ

> መልስ ሰጪ በአዋጅ ቁጥር 293/63 አንቀጽ 4 መሰረት የውጭ አገር ንግድ ፈቃድ እንዲሰጥ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7 መሰረትና በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 224/64 አንቀጽ 9 መሰረት ደግሞ የሰጠውን የንግድ ፈቃድ እዲሰርዝ በግልጽ ስልጣን ተሰጥቷል፡፡....ከላይ ከተጠቀሱት ሕጎች መረዳት የተቻለውም የንግድ ፈቃድ መስጠትም ሆነ መሰረዝ ለንግድ ሚኒስቴር የተሰጡት አስተዳደራዊ ጉዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ መልስ ሰጪ በዚህ ስልጣኑ ተጠቅሞ የይግባኝ ባይ የንግድ ፈቃድ እንዲሰረዝ ወይም እንዲታገድ በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ ይህ ፍርድ ቤት ተቀብሎ የሚያይበት ምክንያት ባለመኖሩ ይግባኝ ባይ .... ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

በማለት ወስኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በከሳሽ የኦጋዴን በጎ አድራጎት ድርጅት/ማህበር እና በተከሳሽ የፍትህ ሚኒስቴር መካከል በነበረው ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ አካባቢ 7ኛ ፍትሐብሔር ችሎት በፍ/መ/ቁ. 19645 ሰኔ 17 ቀን 1994 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ

> ማህበሩ እንዲፈርስ [በተከሳሽ] በተወሰነው ውሳኔ ላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔውን ለማገድ የሚችለው [የፍትህ] ሚኒስትሩ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጡበት

ጊዜ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ የሚኒስትሩ ውሳኔ በሕጉ መሰረት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም ብሎ የመጨረሻ ውሳኔውን መሻር ወይም ማጽደቅ የሚችልበት የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ጠበቃ የሚኒስትሩ ውሳኔ በሕግ መሰረት ያልተሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ሊቀበለው አይገባም ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበለውም፡፡በፍ/ሕ/ቁ 462(3) መሰረት ፍርድ ቤቱ የውሳኔውን አፈጻጸም ሊያዘገየው የሚችለው ለሚኒስትሩ የቀረበው ይግባኝ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ስለሆነና ተጠሪ ይግባኙን በማጽናት የፍትህ ሚኒስትሩ ውሳኔ የሰጡ ለመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ሚያዝያ 10 ቀን 1994 ዓ.ም የሰጠውን የእግድ ትእዛዝ አንስቷል፡፡

በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ጉዳይ የከሳሽ ዋነኛ ክርክር የነበረው በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሚገኘው የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት በሚሰጠው የእገዳ/ስረዛ ትእዛዝ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ሰምተው የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን የተሰጣቸው የፍትህ ሚኒስትር በማህበራት ምዝገባ ደንብ ቁ. 321/1959 አንቀጽ 16(4) መሰረት በቅሬታው ላይ ውሳኔ ሲሰጡ ውሳኔያቸው ላይ የደረሱበትን ምክንያት በጽሁፍ ማስቀመጥ እነዳለባቸው በህግ ግዴታ ተጥሎባቸው እያለ የጽ/ቤቱን ውሳኔ እንዳጸኑት ብቻ በደፈናው በመግለጽ ማለፋቸው ህግን የሚተላለፍ ነው የሚል ነበር፡፡

በተለይ የአስተዳደር አካላት እንደሁኔታው ለመወሰን ሰፊ ስልጣን (Dicretionary power) በተሰጠበት ሁኔታ ለሚሰጡት ውሳኔ ምክንያት እንዲሰጡ ማድረጉ ስልጣናቸውን የዜጎችን መብት በሚጥስ ሁኔታ እንዳይጠቀሙበት ለማድረግ የራሱ አስተዋጽዖ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል፡፡ በክፍል 2 ስር ተሞክሮዋቸውን ካየነው አገሮች ውስጥ በኔዘርላንድና በዩናይትድ ኪንግደም የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ፍርድ ቤቶች ከሚከልሱባቸው መስፈርቶች አንዱ ለውሳኔዎቹ ምክንያት መሰጠቱን ማጣራት መሆኑ ይታወሳል፡፡ ከላይ የተገለጸውን ጉዳይ ያየው ፍርድ ቤት የፍትህ ሚኒስቴር በተጠቀሰው ጉዳይ ወደ ሰጠው ውሳኔ ስረነገር ሳይገባ ውሳኔው ሕግ አውጭው ባስቀመጠው የስነስርዓት ሁኔታ የተሰጠ መሆኑን በማየት አስፈላጊውን ቢፈጽም ለሕግ መከበር የተሻለ አስተዋጽዖ ይኖረው እንደነበር ይታመናል፡፡

- ከላይ ከተጠቀሰው በተለየ ሁኔታ አንዳንድ ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላት በሰጧቸው ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አይተው የመከለስ ስልጣን በግልጽ ባይሰጣቸውም አጠቃላይ የክለሳ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ

የአስተዳደር አካላት ውሳኔዎችን ሲከልሱ ይታያል። በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ፍትሐብሔር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 72790 በቅርብ የተሰጠው ውሳኔ ለዚህ አቋም በምሳሌነት ሊታይ ይችላል። በዚህ መዝገብ በከሳሽነት የቀረበው ፖል ሬዮስና ልጆቹ ኢትዮጵያ ሊሚትድ ሲሆን በተከሳሽነት የቀረበው ደግሞ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ነው። ከሳሽ ባቀረቡት ክስ የግል ንብረታቸው የሆነውንና በከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በስማቸው የባለቤትነት ደብተር የያዙበትን ቤት "የተከራዩትን ቤት እንዲያስረክቡ" የሚል የ10 ቀን ማስታወቂያ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3)'ን በመጥቀስ እንደሰጣቸው በመጠቆም ተከሳሽ አዋጁን ከሕግ ውጭ በመተርጎም ሁከት እየፈጸመ ስለሆነ እንዲወገድላቸው ፍርድ ቤቱን ጠይቀዋል። ተከሳሽ የቀረበበት ክስ ፍርድ ቤቱ የማየት ስልጣን እንደሌለው፤ ከሳሽ ኪራያቸውን ያልከፈሉ ተከራይ እንደሆኑና ያቀረቡትም የባለቤትነት ደብተር ሕገወጥ በመሆኑ ከሰጠው አካል ጋር እየተነጋገረበት መሆኑን በማንሳት ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ሲመረምር ቆይቶ የካቲት 13 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ብይን በአዋጅ ቁጥር 555/2000 አንቀጽ 6(3) መሰረት ተከሳሹ የኪራይ ግዴታቸውን የማይወጡ ተከራዮችን በራሱ እንዲያስለቅቅ ስልጣን እንደተሰጠው፣ ለዚህም የሚሆን ማስፈጸሚያ መመሪያ በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም ስራ ላይ መዋሉን፣ ይህ ስልጣን ለተከሳሹ በሕግ የተሰጠ ስለሆነ ፍርድ ቤት ጣልቃ የሚገባበት የሕግ ስልጣን እንደሌለ፣ ሆኖም አሁን በቀረበው ጉዳይ ከሳሽ የባለቤትነት ደብተር እንዳቀረቡ፣ ተከሳሽ በተያዘው ጉዳይ የተጠቀሰው ንብረት የባለቤትነት ጉዳይ እልባት እንዳላገኘ ያመኑ መሆኑን፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የሚረጋገጠው ባለስልጣናት በሰጡት የባለቤትነት ደብተር መሆኑን፣ፍርድ ቤቱ በከሳሽ የቀረበውን ደብተር ትክክለኛነት ከሚመለከተው የመንግስት አካል በራሱ ተነሳሽነት በማጣራት ማረጋገጡን እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ ያለ ክርክር በፍርድ

ቤት ክስ በማቅረብ ወይም ለሚመለከተው ባለስልጣን አቅርቦ እንዲታይ ማድረግ እንደሚቻል ከዘረዘረ በኋላ

> አዋጅ ቁጥር 555 [ለከሳሽ] ስልጣን የሚሰጠው የባለቤትነት ክርክር በሌለባቸውና ያከራያቸው ንብረቶቹን በራሱ እንዲያስለቅቅ ብቻ ነው፡፡ ተከሳሹ በአዋጁ አስታኮ ለረጅም ጊዜ በባለቤትነት ሲወሳገብበትና ውሳኔ ሲጠብቅበት የነበረውን ንብረት በእጁ ለማድረግ ያደረገው እንቅስቃሴ ሕገ ወጥ ነው፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ የፈጸመው ድርጊት አዋጁ ከሰጠው ስልጣን በላይ (Ultra Virus) ነው፡፡

በማለት ተከሳሹ በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 የቤት ቁጥር 196 እና 196(1) ላይ የሰጠው የማስለቀቅ ትዕዛዝ እንዲነሳ እንዲሁም ሁከት እንዲወገድ ወስኗል፡፡

ከአዋጅ ቁጥር 555/2000 ድንጋጌዎች ንባብ ለመረዳት እንደሚቻለው ሕግ አውጪው ይህንን አዋጅ በማውጣት ለመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ስልጣን የሰጠው የመንግስት ንብረት በሆኑ ቤቶች ላይ የሚታዩ ኪራይ ያለመክፈል ችግሮችን በተፋጠነ ሁኔታ እልባት በመስጠት የመንግስትን ጥቅም ማስጠበቅ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ሕግ አውጪው በዚህ ሕግ ሊደርስበት ካሰበው አላማ እርቆ በመሄድ ለዜጎች በሕገመንግስቱ ጭምር የተረጋገጠውን የንብረት መብት የሚነካ እርምጃ ለመውሰድ መሞከሩ የሕግ ድጋፍ ያለው አይደለም ለማለት ይቻላል፡፡ በክፍል 2 ስር ተሞክሮዎቸውን ካየነው አገሮች ውስጥ የዚህ አይነቱ የአስተዳደር አካላት ድርጊት በኔዘርላንድ Prohibition against Abuse of Power የሚል መርህ ላይ በመመስረት ፣ በዩናይትድ ኪንግደም ደግሞ Procedural Ultra Virus በሚል ውድቅ ሊደረጉ የሚችልበት እድል መኖሩን ማየታችን ይታወሳል፡፡

በፖ'ል ሬዮስና ልጆቹ ኢትዮጵያ ሊሚትድ ጉዳይ የተሰጠው የተጠቀሰው ውሳኔ የአስተዳደር አካላት ሕግ አውጭው አካል በሕግ ሊያስፈጽም ካሰበው እና ከተሰጣቸው ስልጣን ውጭ በመሔድ የዜጎችን መብት እንዳይጋፉ በገለልተኛ አካል መታየቱ ያለውን ጥቅም እና የአስተዳደር አካላት ውሳኔ

መከለስ ስለመቻሉ ሕግ በገዘምታ ባለፈበት ወቅት ፍርድ ቤቶች ይህን ተግባር ካልፈጸሙ የዜጎች መብት ምን ያህል ሊጎዳ እንደሚችል የሚያሳይ ነው ለማለት ይቻላል።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. ከላይ በቀረቡት ሶስት ውሳኔዎች ይስማማሉ? ለምን? ምክንያት በማቅረብ ያብራሩ።
2. ፖል ሬዮስና ልጆቹ ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ተከራካሪ የነበሩበትን ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የሰጠውን ውሳኔ ለመከለስ የተጠቀመበት መስፈርት ከላይ በክፍል ሁለት ስር ልምዳቸውን ባየነው አገሮች ውስጥ ምን ያህል በጥቅም ላይ ውሏል? ይወያዩበት።

<u>ክፍል አራት</u>

4. <u>የአስተዳደር ውሳኔዎችን የመከለስ አፈጻጸም እና አተረጓጎም ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ሰልጣኞች ይህንን ክፍል ተከታትለው ሲያጠናቅቁ፡-

- የአስተዳደር አካላት ውሳኔን ከመከለስ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ የአፈጻጸምና የትርጉም ችግሮችን ይለያሉ፣

- የአስተዳደር አካላት ውሳኔን በመከለስ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዱ ተመራጭ የሆኑ አሰራሮችን ወይም አተረጓጎሞችን ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ይኖራቸዋል፡፡

በዘመናችን የሚገኙ በርካታ ሕገመንግስቶች በሶስቱ የመንግስት አካላት (ሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተርጓሚ) መካከል የስልጣን ክፍፍል ማድረጋቸው የሚታወቅ ነው፡፡ በተጠቀሱት የመንግስት አካላት መካከል አንዱ አንዱን የመቆጣጠር (Check and balance) አሰራር በተወሰነ ደረጃ በተለያዩ አገራት እየተሰራበት የሚገኝ ቢሆንም ቁጥጥሩ በሶስቱ የመንግስት አካላት መካከል የተደረገውን የስልጣን ክፍፍል በማያፋልስ መልክ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በመደበኛ የዳኝነት አካላት ከመከለስ ጋር መተያያዘ ከሚታዩ ችግሮች ውስጥ አንዱ የተወሰኑ ፍርድ ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች የሕግ አውጪው በግልጽ ለአስተዳደር አካላት ውሳኔ በተዋቸው ጉዳዮች በመግባት ውሳኔ ለመስጠት መሞከራቸው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከተንጸባረቀባቸው ውሳኔዎች የፌ/ከ/ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 2384 ታህሳስ 15 ቀን 1997 ዓ.ም የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በምሳሌነት ሊታይ ይችላል፡፡ በዚህ በይግባኝ ባይ የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን እና በመልስ ሰጪዎች 1ኛ. አቶ ብርሃኑ ህሩይ 2ኛ. አቶ ከበደ ገ/ማርያም መካከል የተካሄደ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአሁኑ መልስ ሰጪዎች በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው ሲያገለግሉ በቆዩባቸው አመታት ለጡረታ አበል እየተባለ ከደመወዛቸው ከመቶ አራት፣ ከአሰሪው መስሪያ ቤት ደግሞ ከመቶ ስድስት እየተቀነሰ ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ገቢ ተደርጓል የተባለውን ገንዘብ የሲሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ወደነበረበት እንዲመልስ፣የማህበራዊ ዋስትና

ባለስልጣን በበኩሉ ያለአግባብ ከመልስ ሰጪዎች ሂሳብ ወጪ በማድረግ ለት/ቤቱ የሰጠውን ወደነበረበት ሂሳብ ተመላሽ እንዲያደርግ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በተጠቀሰው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ ውሳኔ በሰጠበት ጉዳይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/ 1988 አንቀጽ 11(1) የማህበራዊ ዋስትና መብትንና ጥቅምን በሚመለከት ባለስልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደሆን የተቀመጠውን ወደጎን ያደረገ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በሰበር መ/ቁ 18342 ታይቶ ታሕሳስ 17 ቀን 1998 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ “ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ በመሆኑ ያለቀለት ጉዳይ” እንደሆነ፣“በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤት በስረ ነገሩ ላይ የመዳኘት ስልጣን የሌለው መሆኑ” እንደተረጋገጠ እና ከዚህ አንጻር ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳለበት ተዘርዝሮ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሯል፡፡

የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች ከመከለስ ጋር መተያያዘ የሚታየው ሌላው ችግር የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በግልጽ የመጨረሻ እንደሆነ ባልተቀመጠባቸው ጉዳዮች ጭምር ለፍርድ ቤቶች ግልጽ ስልጣን እስካልተሰጠ ድረስ ማየት አይገባም በሚል የሚያዘው በሌላው ጫፍ ላይ ያለ አቋም ነው፡፡ ለዚህ በምሳሌነት ከላይ በክፍል 3 ስር የምስራቅ ኦሮሚያ አንድነት የጫት ላኪዎች አክሲዮን ማህበር በይግባኝ ባይነት ፤የንግድ ሚኒስቴር ደግሞ በመልስ ሰጪነት በተከራከሩበት ጉዳይ እና የኦጋዴን በጎ አድራጎት ድርጅት ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በተከራከረበት ጉዳይ ክርክሮቹን ያስተናገዱት ፍርድ ቤቶች የያዘውን አቋም ማስታወሱ ይበቃል፡፡

ከላይ ያየናቸው ሁለት ጫፎች የተያዙበት አቋም የአስተዳደር አካላት በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን መስራታቸውን ከማረጋገጥ፣የዜጎችን መብት ከማስከበር አንጻር አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ይታመናል፡፡

በተጨማሪም የአስተዳደር አካላት ውሳኔን መደበኛ ፍርድ ቤቶች የሚከልሱበት ሁኔታ (Judicial Review) በፌዴሬሽን ምክር ቤት ከሚከናወነው የሕጎችን ሕገመንግስታዊነት ለማረጋገጥ መከለስ (Constitutional Review) የተለየ መሆኑ ሊጤን ይገባል፡፡ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ለመከለስ ፍርድ ቤቶች በዋነኛነት መለኪያ አድርገው የሚወስዱት በሕግ አውጪው አካል የወጡ ሕጎችን ሲሆን የሚሰጡትም ውሳኔ የአስተዳደር አካላቱን ውሳኔ ውድቅ በማድረግ ወዘተ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ የሕጎችን ሕገ መንግስታዊነት አጣርቶ የመወሰን ስልጣን በኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 62(1) የተሰጠው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕጎችን በመመርመር ከሕገመንግስቱ የሚቃረኑ ሆነው ካገኛቸው ኢሕገመንግስታዊ መሆናቸውን ይወስናል፡፡ በመሆኑም የአገራችን ፍርድ ቤቶች በህጎች ሕገመንግስታዊነት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን የሌላቸው መሆኑ የአስተዳደር ውሳኔዎችን ሕጋዊነት ከማረጋገጥ ጋር ያለውን ልዩነት በመረዳት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የአስተዳደር አካላት የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች ከመከለስ ጋር መተያያዘ የዳኝነት አካላት ችግሮች ናቸው ተብለው ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ይስማማሉ? ለምን?
2. የአስተዳደር አካላት ውሳኔዎችን ከመከለስ ጋር በተያያዘ የተሻለ ነው የሚሉት አቋም ምን ዓይነት ነው? በምክንያት በማስደገፍ ይብራራ፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ የመጣውን የመንግስት ተግባራት ለማከናወን በሕግ አውጭው አካል በሚወጡ ሕጎች የሚቋቋሙ የመንግስት አካላት በተቋቋሙበት

ሕግ መሰረት መስራታቸው የሚረጋገጥበት የቁጥጥር ስርዓት በበቂ ሁኔታ ካልተዘረጋ የዜጎች መብት ከመጣሱም በላይ የሕብረተሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ የታቀዱ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖሊቲካዊ ፖሊሲዎች አደጋ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ።

በዚሁ መሰረት የአስተዳደር አካላት በስልጣናቸው ልክ መስራታቸውንና የዜጎችን መብቶች አለመጣሳቸውን ለማረጋገጥ በውሳኔያቸው ሕጋዊነት ላይ ቁጥጥር ማድረጉ የአስተዳደር ሕግ ዋነኛ ጉዳይ መሆኑን ለማየት ሞክረናል።

አገራት እንደሚከተሉት የሕግ ስርዓት እና ውስጣዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች የአስተዳደር አካላትን ውሳኔዎች በመከለስ ሕጋዊነታቸውን የሚያረጋግጡ የተለያዩ ስርዓቶችን የዘረጉ ቢሆንም በተዘረጉት ስርዓቶች የተወሰኑ ልዩነቶች ቢታዩም በተለይ የአስተዳደር ውሳኔዎችን ለመከለስ ከሚጠቀሙባቸው መስፈርቶች አንጻር የሚያመሳስሏቸው ነገሮች እንደሚበዙ አይተናል። ልምዳቸውን ባየነው አገራት ሁሉ የዳኝነት አካላት የአስተዳደር አካላት ወደሰጧቸው ውሳኔዎች ስረነር(Merit) ዝርዝር ሳይገቡ ውሳኔዎቹ ሕግን ተከትለው መሰጠታቸውንና በሕግ ከተሰጠ ስልጣን በመተላለፍ ያልተሰጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለዜጎች መብት ጥበቃ የሚያደርጉበት ሁኔታ ስለመኖሩ ለማየት ተሞክሯል።

በአገራችን የአስተዳደር አካላት ውሳኔ በዳኝነት አካላት የሚከለስበትን ዝርዝር ሁኔታ ያካተተ የአስተዳደር ስነስርዓት ሕግ ባይኖርም በተለያዩ ህጎች ስር የዳኝነት አካላት የአስተዳደር አካላት በሚሰጡት ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመስማት ሕጋዊነታቸውን ሊያረጋግጡ የሚችሉበት ሁኔታ ስለመኖሩ አይተናል። የዳኝነት አካላት ይህ ስልጣን በግልጽ ባይሰጣቸውም ሕግ አውጪው በሚያወጣቸው ሕጎች በግልጽ እስካልተከለከሉ ድረስ በተለይም እንደሁኔታው እንዲጠቀሙበት በተሰጣቸው ስልጣን (Discretionary power) በመጠቀም የአስተዳደር አካላት ወደሰጧቸው ውሳኔዎች ስረነር(Merit) ሳይገቡ በሕግ ተርጓሚነታቸው የውሳኔዎች ሕጋዊነት በማጣራት ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የአስተዳደር አካላት በሕግ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚወጡበት ወቅት ፍትሐዊ የሆነ እና የዜጎችን መብት አላግባብ የማይጋፉ ውሳኔዎች ላይ እንዲደርሱ በተለይ ታስቦ በሕግ አውጭው በግልጽ የተቀመጡ የሚመለከተውን ሰው የመስማት፣ ምክንያት የመስጠት የመሳሰሉ የስነስርዓት ጉዳዮች መከበራቸውን ማረጋገጥ የአስተዳደር አካላት በኢፌዲሪ ሕገመንግስት ለተካተተው የሕግ የበላይነት ተገዢ መሆናቸው ጭምር የሚረጋገጥበት በመሆኑ የዳኝነት አካላት ውሳኔዎችን በሚከልሱበት ወቅት በቂ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

II. ዋቢ ጽሁፎች

ሀ. የፍርድ ቤትጉዳዮች

. አቶ ዳምጠው ጉድሬ እና የፍትህ ሚኒስቴር፤ የፍ/ይ/መ/ቁጥር 1965/92.

. የምስራቅ ኦሮሚያ አንድነት ጫት ላኪዎች አክሲዮን ማህበር እና የንግድ ሚኒስቴር፤ የፍ/ይ/መ/ቁጥር 9/87/25/.

. የኦጋዴን በጎ አድራጎት ድርጅት እና የፍትህ ሚኒስቴር፤የፍ/ብ/መ/ቁጥር 19645.

. ፖ'ል ሬዮስና ልጆቹ ኢትዮጵያ ሊሚትድ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ፤የፍ/ብ/መ/ቁጥር 72790.

. የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን እና 1ኛ. አቶ ብርሃኑ ሕሩይ 2ኛ. አቶ ከበደ ገ/ማርያም፤ የሰ/መ/ቁጥር 18342.

ለ.ሕጎች

. የ1987 የኢፌዲሪ ሕገመንግስት፣

. የመድን ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 86/1986፣

. የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅን ከኢፌዲሪ ሕገመንግስት ጋር ለማጣጣም የወጣ አዋጅ ቁጥር 111/1987፣

. የማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 38/ 1988፣

. የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994፣

. የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝን እንደገና ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 272/ 1994፣

. የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992፣

. የፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999፣

. የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 555/2000 እና

. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 ።።

ሐ.መጽሐፎች

. Auby B.J., ”Administrative Law in France”, Administrative Law Of the European Union, Its Member States and the United States(2002)

. Cranston R. “Reviewing Judicial Review,” Administrative Law and Government Action: The Courts and Alternative Mechanisms of Review.(Oxford, Clarendon Press, 1994.)

. Edley F.C., Administrative Law: Rethinking Judicial Control of Bureaucracy,(Newhaven, Yale university press, 1990.)

. Jones B and Katharine Thompson,”Administrative Law in the United Kingdom,”Administrative Law of the European Union. Its Member States and the United States. A Comparative Analysis. (2002)

. Seerden R. and F. Stroink, “Administrative Law in the Netherlands”, Administrative Law Of the European Union, Its Member States and the United States(2002)

. Stroink F., ”Judicial Control of the Administration’s Discretionary Power” Judicial Control: Comparative Essays on Judicial Review,(1995)

. Thompson B., Constitutional and Administrative Law,(London, Blackstone Press Ltd.,3rd edition, 1997.)